# አባሪዎች

## ሠንጠረዥ 1፡- የእርከኖች እና የብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች

| እርከን | የብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች |
|---|---|
| መዳረሻ 1 | አንደኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት |
| መዳረሻ 2 | የመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት |
| 1 | የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት እና የምስክር ወረቀት 1 |
| 2 | የምስክር ወረቀት 2 |
| 3 | የምስክር ወረቀት 3 |
| 4 | ዲፕሎማ/የምስክር ወረቀት 4 |
| 5 | አድቫንስድ ዲፕሎማ/የምስክር ወረቀት 5 |
| 6 | ▪ በአርት ባችለር ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በሳይንስ ባችለር ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በህግ ባችለር ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በእንሰሳት ህክምና ዶክትሬት ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በህክምና ዶክትሬት ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ የቴ/ሙ.ያ ደረጃ 6 እና ተነፃፃሪ |
| 7 | ▪ በአርት ማስተርስ ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በሳይንስ ማስተርስ ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በህግ ማስተርስ ዲግሪ እና ተነፃፃሪ<br>▪ MPhil እና ተነፃፃሪ<br>▪ በእንሰሳት ህክምና ስፔሻሊቲ እና ተነፃፃሪ<br>▪ በህክምና ስፔሻሊቲ እና ተነጻጻሪ<br>▪ የቴ/ሙ.ያ ደረጃ 7 እና ተነፃፃሪ |
| 8 | • የዶክትሬት ዲግሪ (PhD)<br>• ሰብ ሰፔሻሊቲ<br>• የቴ/ሙ.ያ ደረጃ 8 |

1. እያንዳንዱ እርከን በእውቀት፣ ክህሎት እና ብቃት ረገድ በሚጠበቀው የእርከን መግለጫ መመላከት አለበት፡፡
2. ሁሉም የብቃት ማረጋገጫ ዓይነቶች በሚኖራቸው ዓላማና ባህሪ በብቃት ማረጋገጫ መግለጫዎች ይገለፃሉ።

## ሠንጠረዥ 2፡- ከዕውቀት ክህሎትና ብቃት አንፃር ለእርከኖች የተቀመጡ መሠረታዊ መግለጫዎች

| እርከን | እውቀት | ክህሎት | ብቃት (ኃላፊነትና ተጠያቂነትን መውሰድ) |
|---|---|---|---|
| 8 | በሰለጠነበት የሙያ መስክ ከፍተኛውን የእውቀት ጥግ የደረሰ እና በመስኩ አዲስ እውቀት ለመፍጠር የሚያስችሉ ስልቶችና ዘዴዎችን በመጠቀም ለመስኩ አዳዲስ አስተዋፆዎችን ማድረግ፣ ነባሩን እውቀት ማሻሻልና ማዘመን፣ በወቅቱ ያለ የእውቀት መዋቅር እና ንድፈ ሀሳቦች ያላቸውን አንድምታ የሚገነዘብ እና በዚህም በመስኩ አዳዲስ የእውቀት ማፈላለጊያ እና የምርምር መስኮችን በመለየት ባለበት የሙያ መስክም ሆነ በተለያዩ መስኮች መካከል ግንኙነትና ትስስር መፍጠር፤ | ከትምህርት ወይም ስልጠና ዘርፉ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የሚባሉ ክህሎቶች፣ ስልቶችና መሳሪያዎች፣ ተግባራት እና ቁሶችን መጠቀም፣ አዲስ ምርምር ማከናወን፣ አዳዲስ እውቀቶችና ጥልቅ ጽብረቃዎችን ማድረግ፣ በተሳካ ሁኔታ መፍጠር እና አዳዲስ ፈጠራዎችን እንዲሰራጩ ማድረግ፣ የጥናት ግኝቶችን በሚገባ በመተንተን□ በማደራጀትና በመመርመር ትምህርታዊ ውይይቶችን ማጎልበት፣ የተገኙ እውቀቶችና የምርምር ውጤቶች በዓለም አቀፍ መስፈርት መሠረት በገለልተኛ ባለሙያዎች እንዲገመገሙ ማድረግ፤ | ምሁራዊ እና ሙያዊ ተቀባይነት እና ታማኝነት፣ስነ ምግባር የተላበሰ አሰራር እና አመራር ማሳየት እንዲሁም ገዢ የሆነ ሙያዊ ፍረጃ /ውሳኔ/ መስጠት፣ በተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ ስራን መስራት፣ ለውጥን የማነሳሳት ብቃት፣ በማንኛውም ለረጅም ጊዜ የሚከናወን ውስብስብ እና የላቀ የምርምር ስራ ውስጥ ሙሉ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት ወስዶ መስራት፣ የጥናት ውጤቶችን በሚገባ መግለጽ እና ጥልቅ በሆነ ተቺ ውይይት ውስጥ መሳተፍ፡፡ |
| 7 | በመስኩ ያሉ ልዩና ውስብስብ ንድፈ ሃሳቦች እና እውቀቶች በተቀናጀ እና ላቅ ባለ ደረጃ ተገንዝቦ በስራም ሆነ በጥናት ላይ ያሉ የእውቀት ክፍተቶችን፣ የምርምር አቅጣጫዎችን በጥልቀት በመገንዘብ በሰለጠነበት መስክ አዳዲስ የጥናት አቅጣጫዎችን መለየት፡፡ | በአንድ የእውቀት ዘርፍ ያሉ ንድፈ ሃላቦችን ተመራምሮ እና መርምሮ ገለልተኛ አስተሳሰብ በማጎልበት፣ ውስብስብ መረጃዎችን መርምሮ ችግር ፈቺ ምርምር፣ ስነ-ምግባር የተሞላበት አሰራር□ ጥልቅ ትንተና እና ማጠቃለያ መስጠት፡፡ በአዳዲስ ሁኔታዎች ውስጥ እውቀትን በተግባር ላይ ማዋል፣ ሙያዊ አስተያየት የመስጠት ችሎታ ማሳየት፣ ከተለያዩ መስኮች የተገኙ እውቀቶችን በማቀናጀት አዳዲስ የጥናት መስኮችን መጠቆም እና አዳዲስ ስነ ዘዴዎችን ማመላከት፡፡ | ስልታዊ አቀራረብ በሚጠይቁ የተለያዩ ውስብስብ□ ሰፋፊ እና ያልተጠበቁ ሙያዊ ሁኔታዎች ውስጥም ቢሆን አልፎ ራሱም ሆነ የቡድን አባላቱ ለሚያከናውኑት ጥናትና ውጤት ኃላፊነት መውሰድ የሚያስችል የአመራር ብቃት፣ ሙያዊ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ተነሳሽነት እና አዳዲስ ግኝቶችን ማውጣት መቻል፡፡ |

| **እርከን** | **እውቀት** | **ክህሎት** | **ብቃት (ኃላፊነትና ተጠያቂነትን መውሰድ)** |
|---|---|---|---|
| 6 | አጠቃላይ የትምህርት እና ጥናት መስኩ ሰፊ ከባቢ ውስጥ ከፍተኛ እውቀት መያዝና በአንዳንድ ልዩ የዘርፉ ቅርንጫፎች ላይ የተደራጀ ንዑስ ሙያና እውቀት (specialization) የእውቀት ምንጮችን የመለየት ብቃት እና በመስኩ ያሉ ዋና ዋና ሃሳቦች፣ መርሆዎችና ጽንሰ ሃሳቦች፣ ዋና ዋና የምርምር ሰነ ዘዴዎች እና ችግር መፍቻ ስልቶችን መረዳት፤ | የትምህርት ወይም ጥናት መስኩ የሚገኙ እውቀቶች፣ ንድፈ ሃሳቦች እና መርሆዎችን ሳይንሳዊ በሆነ ዘዴ ተጠቅሞ አንድን ወሳኝ ችግር በጥናት እና በመተንተን የተለያዩ መፍትሄዎችን የማፍለቅና የችግሮቹን መፍቻ የመፈለግ ተግባራዊ ችሎታ ማሳየት፣ በዚሁ ረገድ የተወሰነ ምሁራዊ ግለልተኝነት፣ ጥልቅ ማውጠንጠን እና ትንታኔ መስጠት፣ በግልም ሆነ ከክልሎች ጋር በትብብር በሚሰሩ ስራዎች የተለያዩ መሳሪያዎችን፣ የእውቀት፤ የቴክኒክ እና ተግባቦት ክህሎቾችን መጠቀም መቻል፤ | በተወሰነ ድጋፍ እና አቅጣጫ ስራዎችን እና ሂደቶችን በራስ ተነሳሽነት ጀምሮ በራስ ሃላፊነት በመውሰድ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን የሚያስተናግድባቸው ዐውዶች በሚገባ መርምሮ እና አጠናቅሮ የግልም ሆነ የቡድን ስራዎችን፣ ምርምሮችን የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጡ ማስቻል፤ |
| 5 | አንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ የትምህርት እና ስልጠና ዘርፎች ሰፊ እውቀት ማሳየት፣ በርካታ ቴክኒካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ በፈርጅ በፈርጁ የማደራጀት እና ሰፊ ይዘት ያለው የመረጃ ትንተና እና ቅንጅት መፍጠር፤ | የተለያዩ ዐውደ ሰፊ እና የተለያዩ እውቀቶችን፣ መሳሪያዎችን እንዲሁም ቴክኒካዊ ተግባቦታዊ ክህሎቶችን እንደ ሁኔታው መርጦ በመጠቀም ላልተጠበቁ ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ የመስጠት ክህሎትን ማሳየት፤ | የእለት ተእለት ተግባራት እና የእለት ያልሆኑ ተግባራትን በማስተባበር (በማቀናጀት) በሙያ ዘርፍ እና/ ወይም በኘሮፌሽናል ዐውድ ውስጥ በተለዋዋጭ ሁኔታዎች ውስጥ በመስራት በራስም ሆነ በቡድን ስራ ለሚገኙ ውጤቶች ሃላፊነት መውሰድ፡፡ |
| 4 | አንድ የትምርት ወይ የጥናት መስክ ሰፊና ትርጉም ያለው እውቀት መያዝ መረጃዎችን በሚገመት እና መደበኛ ፎርማት የመተንተን ችሎታ እንዲሁም ዋና ዋና መርሆዎች፣ ንድፈ ሃሳባዊ ጽንሰ ሃሳቦችን እና ረቂቅ አሳቤዎችን ማሳየት፤ | ቴክኒካዊ፤ ሙያዊና የክህት አመማጮችን፤ ተገቢ መሳሪያዎችን፤ ዘዴዎችን እና ቴክኖጂዎችን ተጠቅሞ በተለያዩ ተለዋዋጭ እና ያልተለመዱ ችግሮች መፍትሂ መስጠት፣ የተሰበበሰቡ መረጃዎችን አስተማማኝነት በመመርመር እና ወይም የአሰሪን መመሪያ ተከትሎ አስተማማኝ ስራ መስራት እና ግዴታን መወጣት፤ | የተወሰኑ መደበኛ የአሰራር ስልቶችን እና መስሪያ መሳሪያዎችን በሚጠቀሙ ተገማች እና ውስን ነገር ግን ሰፊ አንድምታ ባላቸው አውዶች ውስጥ በሰፊ አቅጣጫ ሰጪ መርሆዎች ውስጥ አስቀድሞ በታወቁ የአሰራር መስፈርቶች መሪነት ራስን ችሎ በተምሳሌትነት መስራት፣ ስራን መቆጣጠር፣ መገምገም እና በተሰሩ ስራዎች ላይ በሰው አጋዥነት ማንጸባረቅ ወይም በመመሪያ ታግዞ መስራት፤ |

| እርከን | እውቀት | ክህሎት | ብቃት (ኃላፊነትና ተጠያቂነትን መውሰድ) |
|---|---|---|---|
| 3 | በአንድ የተወሰነ የትምህርት ወይም ስልጠና ዘርፍ አጠቃላይ እውቀት መያዝ፣ ቴክኒካዊ ጽንሰ ሃሳቦችን በመከተል መሰረታዊ የአሰራር ዘዴ መሳሪያ፣ ቁሶች፣ መረጃ እና ቴክኖሎጂ እንዲሁም መረጃን የመመርመር ችሎታና መረጃዎችን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ማሳየት፤ | የተለያዩ የእውቀት፣ የተግባር፣ አስተሳሰብ፣ ቴክኒካዊ እና ተግባብታዊ ክህሎቶችን በመጠ ቀም የተወሰኑ ተገማች እና የማይገመቱ ችግሮችን መፍታት፤ | የተለያዩ ተግባራዊ እና ሃሳባዊ ክህሎቶችን በመጠቀም በሚማሩት ትምህርት፣ በስራ ዓለም እና በህይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች መፍታት፣ ራሳቸውን ማስተዳደር የሚያስችል አቅም እና በተወሰነ የሌላ ሰው ቁጥጥር በታወቁና መጠነኛ ተለዋዋጭነት ባላቸው አወዶች ውስጥ ተገቢ መሳሪያዎችን ተጠቅመው በሚሰጧቸው መስፈርቶች መሰረት ስራዎችን መስራት መቻል፣ በግል እና እንደ ቡድን አባል ሃላፊነትን በጋራ የመውሰድ ብቃት፤ |
| 2 | አንድ መስክ መሰረታዊ የአሰራር፣ የእውነታ እና የአሰራር ቅደም ተከተልን እውቀት ይዞ መገኘት እና ተገቢ መረጃዎችን የመጠቀም እና የመተንተን ችሎታ ማሳየት፤ | መካከለኛ የተግባር፣ የአስተሳሰብ እና ተግባቦታዊ ክህሎቶችን እና መሳሪያዎችን ተጠቅሞ አንድን የተለመደ ችግር በታወቁ መፍትሂዎች የመፍታት ብቃት፤ | አንድ ሰው የሚያከናውነው ተግባር በራሱ እና በሌሎች ሰዎች ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት የመረዳት ችሎታ፣የተለመዱ የየእለት ተግባራትን በተቀናጀ መንገድ እና በመጠነኛ ቁጥጥር በሚገመት መልኩ መስራት መቻል እና መጠነኛ የግል ውሳኔ በማሳለፍ የስራ ወጤቶችን ብዛት እና ስራ በተመለከተ የተወሰነ ድርሻ መውሰድ መቻል፤ |
| 1 | የእለት ተእለት ህይወት የሚያገለግል መጠነኛ መሰረታዊ ተግባራዊ እውቀት እና ግንዛቤያዊ ክህሎት ይዞ መገኘት እና ተጨማሪ ትምህርት እና መጠነኛ ስራ መስራት መቻል። | የተለመዱና እምብዛም ውስብስብነት የሌላቸውን መሰረትዊ ሂደቶች ለማከናወን የሚያስችል ቴክኒካል፣ ተግባቦታዊ እና የመሳሪያ አጠቃቀም ክህሎት ይዞ መገኘት፤ | በተረጋጋ እና መስመር በያዘ የስራ አውድ ውስጥ የታዘዙትን ተደጋጋሚነት ያለው ስራ ወጥነት ባለው ሁኔታ ተቆጣጣሪዎች ባሉበት ማከናወን መቻል፤ |

| እርከን | እውቀት | ክህሎት | ብቃት (ኃላፊነትና ተጠያቂነትን መውሰድ) |
|---|---|---|---|
| መደረሻ 2 | ለተጨማሪ ትምህርትና ሥልጠና በሚያዘጋጁ በርካታ ርዕስ ጉዳዮች ላይ መሰረታዊ እውቀትን መገብየት፤ | ቀላል መመሪያዎችን መከተል እና አንዳንድ መሰረታዊ ክህሎቶችን የሚጠይቁ ተያያዥ መሳሪያዎችን እና መሳሪያዎችን በመጠቀም ቀላል ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ተግባራትን ማከናወን ይችላሉ | በሚሰጥ መመሪያ መሰረት ስራዎችን ለማጠናቀቅ አዎንታዊ አመለካከት በመያዝ በትምህርት ቤቱ እና በማህበረሰቡ ውስጥ በገንቢ ሁኔታ መሳተፍ |
| መደረሻ 1 | ለዕለት ተዕለት ዓላማ መሰረታዊ አጠቃላይ ዕውቀት፤ የማስላትና የመፃፍ ተግባር ያከናውናል፤ | መሳሪያዎችን በመጠቀም ልዩ ክህሎት ሳያስፈልግ በመረጧቸው የጉልበት ስራዎች ላይ መሳተፍ መቻል | ከሌሎች ጋር በመተባበር ቀላል እንቅስቃሴዎችን በቅርብ ክትትል እና ቀጣይነት ባለው መመሪያ ስር ማከናወን |

## ሠንጠረዥ 3፡- ለብቃት ማረጋገጫዎች ከተለያዩ መስፈርቶች አንፃር የተቀመጡ መግለጫዎች

| የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት | ባህሪያትና ዓላማ | ብቃቱን ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች | የመግቢያ መስፈርት | የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል | እውቅና የሚሰጠው አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| ሶስተኛ ዲግሪ/ደረጃ 8 | ዶክትሬት ከማስተርስ ዲግሪ ባለፈ የሚጀምር ትምህርት ቀደም ተከተል መደምደሚያ ነው፡፡ የትምህርት ኮርሶችን ሊጨምር የሚችል እና በክትትል ስር ለጥናቱ መስክ እውቀት ከፍተኛ እና የመጀመሪያ አስተዋፅኦ የሚጠይቅ የምርምር ዲግሪ ሲሆን ለዕውቀት የሚያበረክተው አስተዋፅኦ በዘመኑ ለምርምር ሥራ ዓለም አቀፍ መስፈርቶችን ተግባራዊ በማድረግ ላይ ያሉ ነፃ ዓለም አቀፍ ባለሙያዎች ይፈርዳሉ፡፡ ለዶክትሬት ሽልማት የሚያደርሰው የስራ አካል የፅሑፍ እና የህትመት ስራዎችን ያካትታል፡፡ | እንደሙያው ዓየነት የሚለያይ ቢሆንም የዶክትሮት ዲግሪ በደረጃ 8 ቢያንስ 240 ECTS/ 136 ክሬዲት ያስፈልገዋል፤ | የማስተርስ ዲግሪ እና ተመጣጣኝ | የዶክትሬት ዲግሪ ሊሰጥ የሚችለው በአገሪቱ ውስጥ ጥራት እንዲያረጋገጥ ስልጣን በተሰጠው አካል እውቅና በሚሰጠው የትምህርትና ስልጠና ተቋም ብቻ ነው። | ብቃት ማረጋገጫው የሚመራው ፕሮግራም የሚዘጋጀው በከፍተኛ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ሲሆን ጥራት አረጋጋጩ አካል እውቅና ይሰጣል፡፡ |

| የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት | ባህሪያትና ዓላማ | ብቃቱን ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች | የመግቢያ መስፈርት | የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል | እውቅና የሚሰጠው አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| ሁለተኛ ዲግሪ/ ደረጃ 7 | በማስተርስ የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ዲግሪዎች በመደበኛነት በብቃት ደረጃ ዋና ርዕስ ጉዳይ ላይ ለመገንባትና ለእውቀት እድገት አስተዋጽኦ ሊያበረክቱ የሚችሉ ተመራማሪዎችን ለማዘጋጀት የተዘጋጁ ናቸው፡፡ የማስተርስ ዲግሪ ውስጠ -ጥናት ጉልህ ክፍል ሊኖረው ይችላል፡፡ የዚህ ምርምር ውጤት አብዛኛውን ጊዜ በምርምር ጽሑፍ ላይ ይካተታል፡፡ የሚሰራው ምርምር በንድፈ ሃሳብ ረገድ የተራቀቀ ርዕሰ ጉዳይ እና በራስ የመመራት ችሎታ እንዳለው ማሳየት ይኖርበታል፡፡ | እንደሙያው ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም የማስተርስ ዲግሪ በደረጃ 7 ከ120-180 ECTS/ 74-102 ክሬዲት ያስፈልገዋል፡፡ | የባችለር ዲግሪ እና ተመጣጣኝ | ማስተርስ ዲግሪ ሊሰጥ የሚችለው በአገሪቱ ውስጥ ጥራት እንዲያረጋግጥ ስልጣን በተሰጠው አካል እውቅና በሚሰጠው የትምህርትና ስልጠና ተቋም ብቻ ነው፡፡ | ወደ ብቃት ማረጋገጫው የሚመራው ፕሮግራም የሚዘጋጀው በከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሲሆን ጥራት አረጋጋጩ አካል እውቅና ይሰጣል፡፡ |
| የመጀመሪያ ዲግሪ /ደረጃ 6 | አንድ ባችለር ዲግሪ ሰፊ እውቀት፣ ሀሳቦች፣ መርሆዎች፣ ጽንሰ -ሃሳቦች፣ ዋና ዋና የምርምር ዘዴዎች እና አንድ እውቅና ያለው ዋና ርዕሰ ጉዳይ ችግር ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችና ስርዓትን ይጠቀማል። እነዚ ተመራቂዎችን ለከፍተኛ ጥናት እንዲሁም በዲግሪው ዋና ርዕሰ ጉዳይ ላይ ምርምርና ሙያዊ ተግባራትን ለመምራት ያዘጋጃል፡፡ | እንደሙያው ዓይነት የሚለያይ ቢሆንም አንድ ባችለር ዲግሪ/6 ቢያንስ 146 ክሬዲት ያስፈልገዋል፡፡ ለደረጃው ከሚፈለገው ክሬዲት ውስጥ ቢያንስ 50 ክሬዲት በደረጃ 6 መሆን አለበት። | የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰደና ለደረጃው በወቅቱ የተቀመጠውን የመቁረጫ ነጥብ ያሟላ እንዲሁም ከመምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጆችና ተቋማት በደረጃ 5 እና 4 ተመርቀው ችሎታቸው በምዘና የተረጋገጠላቸው አመልካቾች | እውቅና የተሰጣቸው ከፍተኛ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት | ወደ ብቃቱ የሚወስደው መርሃ ግብር በሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎች ተሳትፎ የተዘጋጀ እና የቴክኒክ፣ የሙያ፣ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች የጸደቀ ነው። ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ናቸው። ግምገማዎች የሚሰጡት በብቃት ማእከል ነው። |

| የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት | ባህሪያትና ዓላማ | ብቃቱን ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች | የመግቢያ መስፈርት | የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል | እውቅና የሚሰጠው አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| አድቫንስድ ዲፕሎማ/ ደረጃ 5 የምስክር ወረቀት | ደረጃ V አድቫንሰድ ዲፕሎማ በአንድ የተወሰነ መስክ ውስጥ የንድፈ ሃሳብ እና /ወይም የቴክኒክ ዕውቀት ችሎታ ያላቸው ግለሰቦች ብቁ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው። | የስልጠናው ፕሮግራም የተቀመጠውን ብቃት ስጤት ሲረጋገጥ | 12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰደና ለደረጃው በወቅቱ የተቀመጠውን የመቁረጫ ነጥብ ያሟላ እንዲሁም የደረጃ አራት የምስክር ወረቀትና ተመጣጣኝ | በዘርፍ ጥራት እንዲያረጋግጥ እውቅና በሚሰጠው አካልወይም ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበርበክልል የሙያ ብቃት ምዘና ኤጀንሲዎች | ወደ ብቃቱ የሚወስደው መርሃ ግብር በሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎች ተሳትፎ የተዘጋጀ እና የቴክኒክ፣ የሙያ፣ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች የጸደቀ ነው። ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ናቸው። ግምገማዎች የሚሰጡት በብቃት ማእከል ነው። |
| በዲፕሎማ/ ደረጃ 4/ የምስክር ወረቀት | ደረጃ IV ዲፕሎማ የስፔሳሊስት ዕውቀትን ለመተግበር እና በሰፊ ወይም በልዩ መስክ አካባቢዎች የተካኑ ስራዎችን ወይም ጥናታዊ ስራዎችን ወይም ጥናቶችን ለመስራት ብቁ የሆኑ ግለሰቦችን፤ በአንድ የተወሰነ የሥራ ወይም የጥናት መስክ ውስጥ እውቀትና ክህሎት ያላቸው ግለሰቦች የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በማስተማር ረገድ የላቀ ችሎታ ወይም ሙያዊ ስራ እንዲሰሩ ያዘጋጃቸዋል፡፡ | የስልጠና ፕሮግራም ብቃት ስኬት ሲረጋገጥ እንዲሁም ለመምህርነት ሙያ ለደረጃው ከተቀመጠው ውስጥ 60 ክሬዲቶች ወይም በላይ በደረጃ 4 ወይም ከዚያ በላይ የተቀመጠውን ክሬዲት | 12 ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰደና ለደረጃው በወቅቱ የተቀመጠውን የመቁረጫ ነጥብ ያሟላ እንዲሁም የደረጃ ሶስት የምስክር ወረቀትና ተመጣጣኝ | ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበርበክልል የሙያ ብቃት ምዘና ኤጀንሲዎች | ወደ ብቃቱ የሚወስደው መርሃ ግብር በሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎች ተሳትፎ የተዘጋጀ እና የቴክኒክ፣ የሙያ፣ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች የጸደቀ ነው። ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ናቸው። ግምገማዎች የሚሰጡት በብቃት ማእከል ነው። |

| የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት | ባህሪያትና ዓላማ | ብቃቱን ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች | የመግቢያ መስፈርት | የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል | እውቅና የሚሰጠው አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 3 የምስክር ወረቀት | የደረጃ III የምስክር ወረቀት ለተጨማሪ ጥናት በመስኩ/ በስራ መስኮችና/ ወይም በዝግጅት ዙሪያ በተለያየ ሁኔታ ለተወሰኑ ሚናዎች ሰፊ የዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ግለሰቦች ብቁ ያደርገዋል።በአንድ የተወሰነ የሥራ ወይም የጥናት መስክ ውስጥ እውቀትና ክህሎት ያላቸው ግለሰቦች የቅደመ አንደኛ ትምህርት ቤቶችን በማስተማር ረገድ የላቀ ችሎታ ወይም ሙያዊ ስራ እንዲሰሩ ያዘጋጃቸዋል፡፡ | የስልጠናው ኘሮግራም ለደረጃው የተቀመጠውን ብቃት ስኬት ሲረጋገጥ። | 12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰደና ለደረጃው በወቅቱ የተቀመጠው የመቁረጫ ነጥብ ያሟላ እንዲሁም የደረጃ ሁለት ምስክር ወረቀትና ተመጣጣኝ | ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበርበክልል የሙያ ብቃት ምዘና ኤጀንሲዎች | ወደ ብቃቱ የሚወስደው መርሃ ግብር በሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎች ተሳትፎ የተዘጋጀ እና የቴክኒክ፣ የሙያ፣ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች የጸደቀ ነው። ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ናቸው። ግምገማዎች የሚሰጡት በብቃት ማእከል ነው። |
| ደረጃ 2 የምስክር ወረቀት | ደረጃ II ሰርተፍኬት ለአንድ መስክ /መስኮች የመግቢያ እውቅና ክህሎት ያላቸው ግለሰቦች በዋናነት የዕለት ተዕለት ስራ ወይም ተጨማሪ ጥናት እንዲያከናውኑ ብቁ ያደርጋል፡፡ | ለደረጃው የተቀመጠው ብቃት ስኬት ሲረጋገጥ | 12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ፈተና የወሰዱና ለደረጃው በውቅቱ የተቀመጠው የመቁረጫ ነጥብ ያሟላ እንዲሁም የደረጃ አንድ የምስክር ወረቀትና ተመጣጣኝ | ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበርበክልል የሙያ ብቃት ምዘና ኤጀንሲዎች | ወደ ብቃቱ የሚወስደው መርሃ ግብር በሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎች ተሳትፎ የተዘጋጀ እና የቴክኒክ፣ የሙያ፣ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች የጸደቀ ነው። ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ናቸው። ግምገማዎች የሚሰጡት በብቃት ማእከል ነው። |

| የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት | ባህሪያትና ዓላማ | ብቃቱን ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች | የመግቢያ መስፈርት | የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል | እውቅና የሚሰጠው አካል |
|---|---|---|---|---|---|
| ደረጃ 1 የምስክር ወረቀት | ደረጃ 1 ስርተፍኬት ለአንድ መስክ/ መስኮች የመግቢያ እውቅና ክህሎት ያላቸው ግለሰቦች በአብዛኛው የዕለት ተዕለት ስራ ወይም ተጨማሪ ጥናት እንዲያከናውኑ ብቁ ይሆናሉ፡፡ | ለደረጃው የተቀመጠውን ብቃት ስኬት ሲረጋገጥ | 11ኛ ክፍል የቴ/ሙ.ያ ስልጠና ወስደው ወደ 12ኛ ክፍል ያለፉና በምዘና የተረጋገጠላቸው | ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመተባበርበክልል የሙ.ያ ብቃት ምዘና ኤጀንሲዎች | ወደ ብቃቱ የሚወስደው መርሃ ግብር በሚመለከታቸው ኢንዱስትሪዎች ተሳትፎ የተዘጋጀ እና የቴክኒክ፣ የሙ.ያ፣ የትምህርት እና የስልጠና ተቋማትን በሚመሩ የክልል ቢሮዎች የጸደቀ ነው። ተቋማት በትምህርትና ስልጠና ባለስልጣን እውቅና የተሰጣቸው ናቸው። ግምገማዎች የሚሰጡት በብቃት ማእከል ነው። |
| የ12ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት | የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የምስክር ወረቀት ግለሰቦች የትምህርት ዓይነቶችን ወይም የስልጠና ዘርፎችን እንዲመርጡ፣ ዩኒቨርሲቲ ለመግባት እንዲያመለክቱ እና ወደ ሥራ ዓለም እንዲቀላቀሉ ያደርጋል። | ዕውቀት፣ ክህሎትና ብቃት | 11ኛ ክፍል ጨርሰው ወደ 12ኛ ክፍል ማለፉ የተረጋገጠ | የትምህርት ሚኒስቴር እና የትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች አገልግሎት | ትምህርት ቤቶች በክልል የትምህርት ቢሮዎች እውቅና የተሰጣቸው ይሆናል።<br><br>ምዘና የሚከናወነው በትምህርት ምዘና እና ፈተናዎች አገልግሎት/በትምህርት ሚኒስቴር ነው |

| የብቃት ማረጋገጫ ዓይነት | ባህሪያትና ዓላማ | ብቃቱን ለማግኘት የሚጠበቁ መስፈርቶች | የመግቢያ መስፈርት | የብቃት ማረጋገጫውን የሚሰጠው አካል | እውቅና የሚሰጠው አካል |
| --- | --- | --- | --- | --- | --- |
| መዳረሻ 2 የምስክር ወረቀት | የመካከለኛ ደረጃ የምስክር ወረቀት ግለሰቦች የተጨማሪ ጥናትና ስልጠና መስክ በመምረጥ ፍላጎታቸውንና አቅማቸውን ለይተው ለማወቅና ለመከታተል ብቁ እንዲሆኑ ወይም ልዩ ችሎታ በማያስፈልጋቸው የሥራ ዓለም ውስጥ መግባት | በወቅቱ በሚወሰነው ክልላዊ የማለፊያ ነጥብ ማምጣቱ ሲረጋገጥ | ሰባተኛ ክፍል ያጠናቀቁ እና ወደ 8ኛ ክፍል ማለፋቸው የተረጋገጠ | በክልል ት/ቢሮ ጥራት እንዲያረጋግጥ እውቅና የተሰጠው | ወደ ብቃቱ የሚያደርሰው ማዕቀፍ በትምህርት ሚኒስቴር የሚዘጋጅ ሲሆን የትምህርት ቤቶች ጥራት ማረጋገጫ በክልል ት/ቢሮ ይሰጣል፡፡ |
| መዳረሻ 1 የምስክር ወረቀት | የመጀመሪያ ደረጃ የምስክር ወረቀት ግለሰቦች ለተጨማሪ ጥናትና ስልጠና መስክ ለማወቅና ለመከታተል ብቁ እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። | በወቅቱ በሚወሰነው ክልላዊ የማለፊያ ነጥብ ማምጣቱ ሲረጋገጥ | አምስተኛ ክፍል ያጠናቀቁ እና ወደ 6ኛ ክፍል ማለፋቸው የተረጋገጠ | በክልል ት/ቢሮ ጥራት እንዲያረጋግጥ እውቅና የተሰጠው | ወደ ብቃቱ የሚያደርሰው ማዕቀፍ በትምህርት ሚኒስቴር የሚዘጋጅ ሲሆን የትምህርት ቤቶች ጥራት ማረጋገጫ በክልል ት/ቢሮ ይሰጣል፡፡ |